በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር Ref.No 7/21/12/49
ቀን Date 23/2/2013

ለገቢዎች ሚኒስቴር
ለጉምሩክ ኮሚሽን
ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ለግብርና ሚኒስቴር
ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ንብረታቸው ለወደመባቸው ባለሀብቶች ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 6 ቀን 2013 ዓ.ም ባካሄደው 89ኛ መደበኛ ስብሰባ ውሳኔ ያስተላለፈ ሲሆን፣ ምክር ቤቱ በዚሁ ውሳኔ በየጊዜው የሚቀርቡ የድጋፍ ጥያቄዎችን በዘላቂነት መፍታት የሚያስችል የአሠራር መመሪያ የገንዘብ ሚኒስቴር እንዲያዘጋጅ መመሪያ ሰጥቷል።

ስለዚህ በምክር ቤቱ ውሳኔ መሠረት በመ/ቤታችን የተዘጋጀውን የአሠራር መመሪያ ለአፈፃፀም እንዲረዳ ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
ለክቡር የፊሲካል ፖሊሲና ፐብሊክ ፋይናንስ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ
ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

Letter Hab/GT

ስልክ Tel 251- 11- 155 24 00,22 66 98
251- 11- 155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

# የገንዘብ ሚኒስቴር

## በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ንብረታቸው ለወደመባቸው ባለሀብቶች ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ

ገንዘብ ሚኒስቴር

2013 ዓ.ም

## መመሪያ ቁጥር 69/2013

## በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ንብረታቸው ለወደመባቸው ባለሀብቶች ድጋፍ ስለሚደረግበት ሁኔታ የወጣ መመሪያ

### 1. አውጪው ባለሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስቴር የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 6 ቀን 2013 ዓ.ም. ባካሄደው 89ኛ መደበኛ ስብሰባ በሰጠው ውክልና መሠረት ከዚህ የሚከተለውን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 2. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ንብረታቸው ለወደመባቸው ባለሀብቶች በመንግሥት ስለሚደረግ ድጋፍ የወጣ መመሪያ ቁጥር 69/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 3. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ "የተፈጥሮ አደጋ" ማለት አግባብ ባለው የመንግሥት አካል በሚረጋገጥ ለበርካታ ዓመታት አጋጥሞ በማያውቅ ሁኔታ በደረሰ ከፍተኛ የጐርፍ አደጋ ምክንያት በንግድ እና ኢንቨትመንት ሥራ ላይ በተሠማሩ ባለሀብቶች ንብረት ላይ የደረሰ አደጋ ነው፡፡

2/ "ሰው ሠራሽ" ማለት በአገራችን የተለያዩ ክፍሎች በሚፈጠር ያለመረጋጋት ምክንያት በንግድ እና በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ በተሠማሩ ባለሀብቶች ንብረት ላይ የደረሰ አደጋ ነው፡፡

3/ "ንብረት ላይ የደረሰ አደጋ" ማለት በንግድ ወይም በኢንቨስመትን ሥራ ከተሠማራው ባለሀብት ንብረት ውስጥ በዋጋ ቢያንስ ከንብረቱ ዋጋ ውስጥ 25% እና ከዚያ በላይ ውድመት ያጋጠመው ከሆነ ነው፡፡

4/ "ባለሀብት" ማለት በንግድ፣ በኢንዱስትሪ በግብርና ወይም በአገልግሎት ዘርፍ በየትኛውም የአገሪቱ ክልል የተሠማራ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

### 4. የመመሪያው ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ጉዳት የደረሰባቸው ባለሀብቶች ከመንግሥት በሚደረግላቸው ድጋፍ ሥራቸውን መቀጠል እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2
ሚኒስቴር

## 5. የድጋፉ ተጠቃሚዎች

በዚህ መመሪያ የተቋቋመው ድጋፍ ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት፣

1/ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበትን ንብረታቸውን በመተካት ሥራቸውን ለመቀጠል ፈቃደኛ የሆኑ እና ለዚህም ውል የገቡ፣

2/ ከ2008 ዓ.ም. ጀምሮ በአገሪቱ በተፈጠረ ወይም በሚፈጠር ያለመረጋጋት ምክንያት በንብረታቸው ላይ ጉዳት የደረሰና የደረሰውን ጉዳት ለመተካት ከዚህ ቀደም ድጋፍ ያልተደረገላቸው፣

3/ ለደረሰባቸው ጉዳት ማካካሻ የሚውል ሙሉ የካሣ ክፍያ ከኢንሹራንስ ተቋም ያላገኙ፣

ባለሀብቶች ናቸው፡፡

## 6. በንግድ ትርፍ ግብር ረገድ የሚደረግ ድጋፍ

### 6.1 የግብር እፎይታ ጊዜያቸውን ያላጠናቀቁ ባለሀብቶች

በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ የተፈቀደውን የግብር እፎይታ ጊዜ ያላጠናቀቁ ከሆነ፣ በመደበኛ ሁኔታ ላጋጠማቸው ኪሣራ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ መሠረት የማበረታቻው ዘመን ግማሽ ለሚሆን ጊዜ ያጋጠማቸውን ኪሣራ የማሸጋገር መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

i) በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ሥራቸውን ለማከናወን ባለመቻላቸው ምክንያት ያጋጠማቸው የእያንዳንዱ ዓመት ኪሣራ፣ የእፎይታው ጊዜ ከተጠናቀቀበት ዓመት ቀጥሎ ላሉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት እንዲሸጋገር ይደረጋል፣ ሆኖም ከዚህ ጊዜ በኋላ ይህ ኪሣራ ሊሸጋገር አይችልም፡፡

ii) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6.1(i) መሠረት ኪሣራው ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ብቻ የሚሸጋገር በመሆኑ ከሦስቱ ዓመት መጠናቀቅ በኋላ በእፎይታው ጊዜው ያጋጠመው ኪሣራ በኢንቨስትመንት አዋጁ መሠረት እንዲሸጋገር ይደረጋል፡፡

### 6.2 የግብር እፎይታ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሳያወጡ ሲሠሩ የነበሩ ባለሀብቶች

በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ኪሣራ የደረሰባቸው ባለሀብቶች በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት በመደበኛ ሁኔታ ለሁለት ዓመታት ያጋጠማቸውን ኪሣራ የማሸጋገር መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

i) በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ሥራቸውን ለማከናወን ባለመቻላቸው ምክንያት ያጋጠማቸው የእያንዳንዱ ዓመት ኪሣራ ካጋጠመበት ዓመት ቀጥሎ ላሉት ሦስት ተከታታይ ዓመታት እንዲሸጋገር ይደረጋል፣

ii) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6.2(i) መሠረት ኪሣራው ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ብቻ የሚሸጋገር በመሆኑ ከሦስቱ ዓመት መጠናቀቅ በኋላ የሚሸጋገር ኪሣራ አይኖርም። ሆኖም በኢንቨስትመንት አዋጅ እንዲሁም በገቢ ግብር አዋጁ መሠረት የሚሸጋገረው ኪሣራ ከዚህ ጊዜ መጠናቀቅ በኋላ እንዲሸጋገር ይደረጋል።

## 7. <u>ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ በሚከፈል ታክስ ረገድ የሚደረግ ድጋፍ</u>

በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት በንብረታቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ባለሀብቶች የወደመባቸውን ንብረት ለመተካት ወደአገር የሚያስገቡዋቸው መሣሪያዎች፣ ተሽከርካሪዎች እና ዕቃዎች ወደአገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ከተጣለ ማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ይደረጋል።

## 8. <u>በውዝፍ የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም በተርንኦቨር ታክስ ረገድ ስለሚደረግ ድጋፍ</u>

በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት በንብረታቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ባለሀብቶች ጉዳት የደረሰበትን አመት ጨምሮ ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ላሉት የግብር ዘመናት የሚፈለግባቸው እና ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ያላደረጉት የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርንኦቨር ታክስ በምህረት ቀሪ እንዲሆን ይደረጋል።

## 9. <u>የአገር ውስጥ ብድር ማመቻቸት</u>

በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት በንብረታቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ባለሀብቶች ንብረታቸውን ለመተካት የሚያስችል ብድር የሚያገኙበት ሁኔታ ወይም ለኢንቨስትመንቱ የወሰዱት ብድር የሚሸጋሸግበት መንገድ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሥራ አመራር ቦርድ በኩል ይመቻቻል።

## 10. <u>ባለሀብቶች ሊያቀርቡት የሚገባ ማስረጃ</u>

በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት በንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰበት ባለሀብት፣

1/ በንግድ ወይም በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ ተሠማርቶ የቆየ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፣

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2 ሚኒስቴር

2/ ከነበረው ሀብት 25% እና ከዚያ በላይ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ አደጋው በደረሰ ጊዜ ሪፖርት ከቀረበለት የመንግሥት አስፈፃሚ አካል ፣

3/ በአደጋው ምክንያት ከጥቅም ውጪ የሆነውን ንብረት ዝርዝር ከፀጥታ አካላት ወይም ጉዳዩ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ፣ ማቅረብ አለበት፡፡

## 11. ኮሚቴ ስለማቋቋም

በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት በንብረታቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ባለሀብቶች የሚያቀርቡትን የድጋፍ ጥያቄ እየመረመረ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሀሳብ የሚያቀርብ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

## 12. የኮሚቴው አባላት

የኮሚቴው አባላት ከሚከተሉት የመንግሥት መ/ቤቶች የተውጣጡ ይሆናሉ፡-

| | | |
|---|---|---|
| 1/ | የገንዘብ ሚኒስቴር ተወካይ ........................ | ሰብሳቢ |
| 2/ | የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተወካይ ......... | አባል |
| 3/ | የግብርና ሚኒስቴር ተወካይ ....................... | አባል |
| 4/ | የገቢዎች ሚኒስቴር ተወካይ ..................... | አባል |
| 5/ | የኢትዮጵያ ኢንቬስትመንት ኮማሽን ተወካይ .... | አባል ፀሐፊ |

## 13. የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

1/ ከባለሀብቶች የሚቀርብ የድጋፍ ጥያቄ የሚቀርብበትን አኳኋን፣ የወደመው ንብረት የሚጣራበትን የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

2/ ከባለሀብቶች የሚቀርበውን የድጋፍ ጥያቄ እና የሚቀርበውን ማስረጃ ይመረምራል፣ ተጨማሪ ማስረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ እንዲቀርብ ይጠይቃል፣

3/ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ጉዳት የደረሰበትን የሥራ ቦታ በአካል በመገኘት ይገመግማል፣

4/ ለባለሀብቱ ሊደረግ የሚገባውን ድጋፍ መጠን በሚመለከት ለገንዘብ ሚኒስትሩ የውሣኔ ሀሳብ ያቀርባል፣

የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

## 14. የገቢዎች ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

የገቢዎች ሚኒስቴር በገንዘብ ሚኒስቴር በሚሰጠው ውሣኔ መሠረት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት በንብረቱ ላይ ጉዳት የደረሰበት ባለሀብት፣

ሀ) ያጋጠመው ኪሣራ እንዲሸጋገር ወይም ከሚፈለግበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም የተርንኦቨር ታክስ ነፃ እንዲሆን፣

ለ) ለወደመው ንብረት መተኪያ የሚውሉ መሣሪያዎችን፣ ተሽከርካሪዎችን ወይም ዕቃዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደአገር እንዲያስገባ፣

ያደርጋል፡፡

## 15. ሪፖርት ስለማቅረብ

1/ የገቢዎች ሚኒስቴር በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠውን ድጋፍ መጠን የሚያሳይ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካል፡፡

2/ የገንዘብ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚላክለትን ለባለሀብቶች የተደረገውን ድጋፍ የሚያሳይ ሪፖርት በየዓመቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

## 16. ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ ከጥቅምት 18 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ጥቅምት 17 ቀን 2013 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*

በተፈ.ጥ.ሰው ሰራሽ አደጋ.WGT